# ኢትዮጵያውያን በሱዳን ግድያና ድብደባ ደረሰባቸው
# (ሌላው ዳርፉር)

## ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
## <u>የተሰጠ መግለጫ</u>

ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ. ም. (July 21, 2008)

ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ውሃ-ገብ ለም መሬት ለሱዳን በድብቅ ከሰጠ ጀምሮ በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በሱዳን ጦር ወረራ የሰው ሕይወትና በሚሊዮን ብር የሚቆጠር ንብረት መጥፋቱን ከአሁን በፊት አስታውቀናል።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ ጥቃት እየተሰነዘረ ያለው በሱዳን አገር ለብዙ ዘመናት በስደት በሚኖሩና ቋሚ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ባላቸው ኢትዮጵያውያን ላይ ነው።

1ኛ ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ. ም.(July 09, 2008) በገዳሪፍ ክፍለ ሀገር፤ እምጉልጃ ከተባለው የስደተኛ ሠፈር የሱዳን ወታደሮች ገብተው በሚከተሉት ሰዎች ላይ ከፍተኛ ድብደባ አድርሰዋል፤

1. አቶ በውቀቱ አስረሱ
2. አቶ ፈንታሁን ብሩ
3. ወይዘሮ የወይን ሐረግ
4. አቶ ዱቤ አስረስ ከ2 ልጆቻቸው ጋር
5. አቶ አብርሃም አዳል
6. አቶ ብርሃኑ
7. ማማ ካሣ ከነ ልጆቻቸው
8. አቶ አምባው እና
9. አቶ ወንድሙ

ከላይ የተዘረዘሩት ሰዎች አንዳንዶቹ ሕክምና አግኝተው የተመለሱ ሲሆን ብዙዎቹ ግን በአሁኑ ጊዜ ሆስፒታል ገብተው በሕክምና ላይ ሲገኙ፤ የእምጉልጃ ከተማ ኗሪ የሆነው ሕዝብ ግን "ለብዙ ዓመታት አብረውን የኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለምን ትደበድባላችሁ፤ ጠረፍ ሔዳችሁ ለምን አትዋጉም" በማለት ወታደሩን በአደባባይ ተናግሯል።

2ኛ ሐምሌ 3 ቀን 2000 ዓ. ም.(July 10, 2008) ከመተማ ማዶ ባለችው ገላባት ከተማ የሱዳን ወታደሮች አሰሳ ወጥተው መንገድ ዳር ላይ ሻይ በመሸጥ ይተዳደሩ የነበሩ 11 (አሥራ አንድ) ኢትዮጵያውያን ሴቶችን በማንገላታትና ከዚያም ለሻይ የጣዱትን ፍል ውሃ በሰውነታቸው ላይ በመድፋት የሚዘገንን ጭካኔ ፈጽመዋል። በዚህ ድርጊቱ የተቆጣው የአካባቢው ኢትዮጵያውያን ወንዶች ደግሞ አፀፋ ለመመለስ በዱላና ቢላዋ ሱዳኖችን እንደወጉ ሲታወቅ፤ ወሬው መተማ ከተማ ሲሰማ ደግሞ ሕዝቡ በቁጣ ተነሣስቶ ከአምስት(5) ባላነሱ የሱዳን ተወላጆች ላይ የሞት አደጋ አድርሷል። በዚህም ምክንያት በሁለቱ ከተሞች ያለው ግንኙነት ለ5 ቀናት ያህል ዝግ ነበር። የሴቶች እህቶቻችንን ሁኔታ ለማወቅ በበለጠ ባማጣራት ላይ ነን።

3ኛ እንጉርጉር፣ አሸኩርና ዶካ በተባሉ ትንንሽ የሱዳን ከተማዎችም ወታደሩ ሌላ የጭፍጨፋ ዘመቻ አካሂዶ ከ30 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ጠፍቷል። የሞቱትን ሰዎች ስም ዝርዝር ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው።

4ኛ በካርቱም፣ በኡምድሩማን እና በባሕሪን ከተማዎች መንግሥታዊ ባልሆኑ የተራድኦ ድርጅቶች የሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የCIA (የአሜሪካ መረጃ ክፍል) ሰላዮች ናችሁ በሚል ሽፋን ካለፉት 3 ወራት ወዲህ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከሥራ በመባረር ላይ መሆናቸው ተረጋግጧል። የዚህ ኢሰብአዊ የሆነ እርምጃ ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከነቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ ችግር ላይ ሊወድቁ እንደሚችሉ ገልፀው እሮሮአቸውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንድናሰማ ተማፅነዋል።

ሰሞኑን በሱዳን ወስጥ ለተካሄደው ጭካኔ መነሻ የሆነው የአገሩ ዳር ድንበር መሰጠትና መደፈር ያስቆጣው የአካባቢው ሕዝብ በትክክል ካልታወቁ የታጠቁ ቡድኖች ጋር በመሆን በቋራ በኩል ከሱዳን ድንበር 24 ኪሎ ሜትር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቆ ገብቶ በሠፈረው የሱዳን ጦር ላይ ከፍተኛ ጥቃት በማድረሱ ነው። ከዚህ ጥቃት በኋላ በነፍስ ገቢያ አካባቢ ሠፍሮ የነበረው የሱዳን ወታደር ሙሉ በሙሉ ለቆ መውጣቱ ተረጋግጧል።

ከዚህ ሌላ የሱዳን ጦር በአርማጭሆ በኩል ደለሎ በሚባል አካባቢ 45 ኪሎ ሜትር የሚሆን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመግባት ለመስፈር ሲዘጋጅ፤ በአካባቢው ሕዝብ ከፍተኛ ጥቃት ደርሶበት ወደ ሱዳን ጥቅልሎ ሲሔድ በመንገድ በሚያገኛቸው ከብቶች ሁሉ ላይ ጥይት በመተኮስ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ከብቶችን መግደሉ ታውቋል። ኢትዮጵያውያን አፀፋውን በሱዳን ባለሀብቶች ላይ ይመልሳሉ ተብሎ በሱዳን በኩል ከፍተኛ ፍርሃት እንዳለ ይነገራል።

ይህ ዓይነት ጭካኔና ጥፋት በሚካሄድበት በአሁኑ ወቅት፤ የወያኔ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዲስ አበባ ውስጥ July 14, 2008 ባወጣው መግለጫ "የኢትዮጵያና ሱዳን ግንኙነት ጤነኛ፣ ጠንካራና በየጊዜው እየተሻሻለ ያለ ነው" ብሏል።

## <u>ውድ ወገኖቻችን ሆይ!</u>

በሱዳን ውስጥና በምዕራቡ ድንበር በኩል በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ጭፍጨፋ፣ ጭካኔና ከፍተኛ ጥፋት የሚደረገው በመለስ ዜናዊ የጥፋት ቡድን አጋርነት ጭምር መሆኑን ብዙ መለኪያዎች ያረጋግጣሉ።

ስለዚህ በየትኛውም የዓለም ክፍል (በውጭ ሀገራት) የምንገኝ ቁጥራችን ወደ ሚሊዮን የምንደርስ ኢትዮጵያውያን የወገኖቻችንን እሮሮና ለዚህም ከፍተኛ ወንጀል በመለስ ዜናዊ ቡድን ተባባሪነት መሆኑን በመግለፅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ማለትም ለወታደሩ፣ ለሚሊሺያው፣ ለሠራተኛው፣ ለፓርላማ አባላት፣ ለወጣቱ፣ ለአረጋውያንንና ለሃይማኖት አባቶች በደብዳቤ፣ በኢንተርኔት፣ በስልክና በሌላም በሚቻለው መንገድ ሁሉ እንድናሰማ ጥሪ እናቀርባለን።

### ኢትዮጵያ በልጆቿ ቆራጥነት ትነሣለች!!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
e-mail:- ethiosudanborder@yahoo.com